# ጠረንሽ ወረረኝ



ነዱ በሰፈሬ ዘወይ በይብኝ
እባክሽን ውዴ ኣትጨክኝብኝ
ቢደረደር መርፌ ኣይሆንም ማረሻ
ቀዳዳው ጠፋብኝ ከፍቅርሽ መሽሻ።



ስምሽን ስጠራው ሆዴ ይዋልላል
'ዋ! ታመልጥህና ይቆጭሃል!' ይላል
ቢደረደር መርፌ ኣይሆንም ማረሻ
እቱ ላንቺ ፍቅር ኣጣሁኝ ማርከሻ።



ግራ፣ ቀኙ ገደል የለውም መንገድ
ካንቺ ተለይቼ ወየት ነው የምሄድ?
ቢደረደር መርፌ ኣይሆንም ማረሻ
ካንቺ ተለይቼ አጣሁኝ መድረሻ።



እስቲ ዓይናን ልየው ደፍሬ፣ ቀርቤ
ሳላያት ከዋልኩኝ ይጨነቃል ልቤ
ቢደረደር መርፌ ኣይሆንም ማረሻ
ፎቶሽን ላኪልኝ ልቤን ማስታገሻ።

ኣብሬያት ኣድሬ ሕልሜ ነው በውኔ
መለየት ኣቃተኝ፣ ወይኔ! ወይኔ!
ቢደረደር መርፌ ኣይሆንም ማረሻ
ጠረንሽ ወረረኝ ሆኖኝ ማስታወሻ።

ገ/ኢ. ጐርፉ።